DISTRICT OF COLUMBIA
OFFICE OF THE STATE SUPERINTENDENT OF
EDUCATION

ውድ ወላጅ ወይም አሳዳጊ፣

በጸደይ 2017 ላይ ልጅዎ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት/ማንበብና መጻፍ (ELA - ኢ.ኤል.ኤ) እና በሂሳብ ትምህርት ለኮሌጅ እና የስራ መስክ ዝግጁነት ለመመዘን አጋርነት (PARCC - ፒ.ኤ.አር.ሲ.ሲ) የተሰኘውን ምዘና ወስዷል/ወስዳለች። በዲሲ ውስጥ በተከታታይ ለሶስተኛ ዓመት፣ የፒ.ኤ.አር.ሲ.ሲ ምዘና ለተማሪዎች የበለጠ አስፈላጊ የሆኑትን እውቀቶች እና ክህሎቶችን ለክቷል - እንደ መጻፍ፣ ጥያቄዎችን መስራት የመሳሰሉትን ክህሎቶችን፣ እና ለሂሳብ እና ለኢ.ኤል.ኤ በራስ መተማመን እና ወደ ስኬታማነት የሚመሩ መሰረታዊ ክህሎቶችን። ልጅዎት ለሚያጠናቅቀው/ለምታጠናቅቀው ለእያንዳንዱ ምዘና የነጥብ ዘገባ ይደርስዎታል።

አባሪ ሆኖ የተያያዘው መመሪያ ከልጅዎት የነጥብ ሪፖርት ሊማሩ የሚችሏቸውን በጣም ጠቃሚ ነገሮች በዝርዝር ያብራራልዎታል፤ በተጨማሪም በቀጣዩ ዓመት ልጅዎ እንዲያሻሽል/እንድታሻሽል የሚያግዙ ግብዓቶችን ያቀርብልዎታል።

የፒ.ኤ.አር.ሲ.ሲ ነጥቦች የልጅዎትን አጠቃላይ የትምህርት ታሪክ እንደማይገልጹ እናውቃለን። ውጤቶቹ ከሌሎች በርካታ መለኪያዎች ጋር በአንድ ላይ በመሆን ማለትም - የሪፖርት ካርድ ደረጃዎች፣ የክፍል ውስጥ ብቃት፣ እና የመምህር ግብረ መልስን ጨምሮ - የልጅዎትን አጠቃላይ የትምህርት መሻሻል ሁኔታ ከሚገልጹ ነገሮች አንዱ ነው። በዚህ ሁኔታ፣ የፒ.ኤ.አር.ሲ.ሲ ምዘና ለእርሶ እና ለልጅዎት መምህራን በክፍል ደረጃ ወይም ኮርስ ላይ ተማሪው/ዋ ባለፈው የትምህርት ዓመት ያደረገውን/ችውን የትምህርት መሻሻል በተሻለ ሁኔታ ለመረዳት እንዲያግዝ ታስቦ የተዘጋጀ ነው።

ተማሪዎች የፒ.ኤ.አር.ሲ.ሲ ምዘና በኢ.ኤል.ኤ እና በሂሳብ ትምህርቶች ይወስዳሉ። በእያንዳንዱ የትምህርት ዘርፍ፣ ነጥቡ ልጅዎ ጥሩ እየሰራባቸው/እየሰራችባቸው ያለበትን/ያለችበትን ቦታዎች ለማሳየት ወይም ተጨማሪ እገዛ የሚያፈልግባቸውን ቦታዎች ለማንፀባረቅ ተከፋፍሏል። ይህ መረጃ አስፈላጊ ሲሆን ተጨማሪ ድጋፍ እንዲሰጡ ወይም ደግሞ የበለጠ ጠንከር ያለ ስራ ለተማሪው እንዲሰጡ የመምህራንን የማስተማር ሂደት ለመምራት ሊያገለግል ይችላል። በተጨማሪም በቤት ውስጥ የመማሪያ ጊዜ ላይ ትኩረት ለማድረግ ሊያገለግል ይችላል።

ግባችን በዋናነት ሁሉም ተማሪዎች በትምህርታቸው ስኬታማ መሆናቸውን እና ህልማቸውን እና ምኞታቸውን ለማሳካት መቻላቸውን ማረጋገጥ ነው። አጠቃላይ የሆነ ጥያቄ ካለዎት ወይም ደግሞ ስለ ምዘናው የበለጠ መረጃ ከፈለጉ፣ እባክዎትን www.osse.dc.gov/parcc የሚለውን ድህረ ገጻችንን ይጎብኙ ወይም ከልጅዎት መምህር ጋር ውይይት ያድርጉ።

በኦ.ኤስ.ኤስ.ኢ (OSSE) ሁሉም ተማሪዎች በከፍተኛ ደረጃ መማር እና ውጤት ላይ መድረስ እንደሚችሉ የምናውቅ ሲሆን፤ ልጅዎ ስኬታማ እንዲሆን/እንድትሆን በማገዝ ሂደት ከእርስዎ ጋር በአጋርነት ለመስራት ለተሰጠን እድል አድናቆታችንን እንገልጻለን።

አመሰግናለሁ፣
ሃንሶውል ካንግ
የዲሲ እስቴት የትምህርት ዋና ተቆጣጣሪ

# የውጤት ሪፖርትን ማከፋፈል፡ ፊት

ይህ መመሪያ ከልጅዎ የውጤት ሪፖርት ሊረዱ የሚገባዎትን በጣም አስፈላጊ ግንዛቤ እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ይመራዎታል። በመጪው ዓመት ልጅዎ አሰራሩን እንዴት እንደሚያሻሽል ጠቃሚ መረጃዎችን ይሠጥዎታል።



ሂሳብ

ስኮት ቴስታተር
Anywhereመካከለኛ ትምህርት ቤት

የ7ኛ ክፍል ፈተና ውጤቶች
የDC የሕዝብ ትምህርት ቤቶች

ስለዚህ ፈተና

ስኮት የPARCC (ለኮሌጅ እና ለሥራ ዝግጁነት ትብብር) ሂሳብ ፈተና በ2017 ፀደይ ወራት ወስዷል። ...C ተማሪዎችን በጥልቀት እንዲያስቡ፣ ለችግሮችን መፍትሄ እንዲሰጡና ለዚህ ክፍል ወይም ...ት እንዲሁም ለኮሌጅ እና ለሥራ ስኬታማ ለመሆን የሚያስፈልጉ ዕውቀቶችን እና ችሎታዎችን ... ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ ይጠይቃል። እነዚህ ውጤቶች የስኮትን ፍላጎት እና ጥንካሬ ...ት የሚያስችል ከበርካታ መንገዶች አንዱ ነው። በዚህ መረጃ ላይ በመመርኮዝ ወላጆች ...ቸው ምን አይነት መረጃ እንደሚያስፈልጋቸው ከአስተማሪዎች እና ከትምህርት ቤት ጋር ሊሰሩ ይችላሉ። ትምህርት ቤቶች የዚህን ሪፖርት መረጃ በመጠቀም ስርዓተ ምህርትንና ማሻሻያዎችን ለመጪው ዓመት ለተማሪዎች የተሻለ እቅድ ሊያወጡ ይችላሉ።

ስለዚህ ሪፖርት ጥያቄዎች ካሉዎት፣ እባክዎን ከስኮት አስተማሪ ወይም ርዕሰ መምህር ጋር ይነጋገሩ ወይም ለDCPS በ**(202) 123-4567**ይደውሉ። ስለPARCC ፈተና ጥያቂዎች ካሉዎት OSSEን በ**(202) 719-6500** ይደውሉ።

ይህንን ሪፖርት እንዴት አድርገው ይጠቀሙበታል?

ይህ ሪፖርት የስኮትን ችሎታዎች እድገት ያለዎትን ጥያቄዎች እንዲመልሱ ይረዳዎታል።

- የስኮት ውጤት እንዴት ነበር?
- በዚህ ትምህርት የስኮት ጥንካሬ እና ድክመት ምንድን ናቸው?
- ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ሲወዳደር የስኮት ውጤት እንዴት ነበር?

በዚህ የሂሳብ ፈተና የስኮት ውጤት እንዴት ነበር?

ይህ ክፍል የተማሪዎን የፈተናውን አጠቃላይ ውጤት ያሳያል። ይህ አጠቃላይ ውጤት የተማሪዎ ችሎታ ደረጃን ይወስናል።

የችሎታ ደረጃ
ደረጃ 4
ውጤት
760

በደረጃ 4 ውጤት ያመጡ ተማሪዎች
የሚጠበቀውን ያህል
ለ 7ኛ ክፍል የመማሪያ መለኪያዎች



- ደረጃ 1 የሚጠበቀውን ገና አለሟላም
- ደረጃ 2 በከፊል የሚጠበቀውን አሟልቷል
- ደረጃ 3 የሚጠበቀውን መቅረብ
- ደረጃ 4 የሚጠበቀውን አሟልቷል*
- ደረጃ 5 ከሚጠበቀው በላይ*

*ደረጃ 4 & 5 ለሚቀጥለው ክፍል ዝግጁ ለመሆናቸው እና የከፍተኛ ትምህርትና ኮሌጅን ለመልቀቅና ለስራ ዝግጁ መሆናቸው ያመለክታል።

የበለጠ ማወቅ ይፈልጋሉ?

የስኮት ውጤቶች ከሌሎች ተማሪዎች ውጤት ጋር ሲወዳደር እንዴት እንደሆነ ለማወቅ እና ስኮት በፈተናው ቁልፍ በሆኑ ክፍሎች ምን ያህል እንደሰራ ለማወቅ የሚቀጥለውን ገጽ ይግለጹ።

## 1) የፈተናው መግለጫ

በሪፖርቱ ጫፍ ላይ አጭር የፈተናው መግለጫ አለ። ስለዚህ ሪፖርት ጥያቄዎች ካሉዎት በዚህ አንቀጽ መጨረሻ ላይ ያለውን አድራሻ ይመልከቱ።

## 2) በጠቅላላ የልጅዎ ውጤት እንዴት ነበር?

የልጅዎ ውጤት ከአምስቱ አንዱ የውጤት ደረጃዎች ውስጥ ይካተታል። የውጤት ደረጃዎቹ የልጅዎ ውጤት ምን ውስጥ እንደሚገባ እና ልጅዎ ለክፍል ደረጃው/ዋ የሚጠበቀውን አሟልቶ/ታ እንደሆን ይጠቁማል። በደረጃ 4 ወይም 5 የሆነ ውጤት ልጅዎ በትምህርቱ የሚጠበቅበትን/ባትን ወይም ከሚጠበቀው በላይ አግኝቷል/ታለች ማለት ነው። በተጨማሪም ለኮሌጅ እና ለሥራ ዝግጁነት ትክክለኛውን አቅጣጫ ይዟል/ዛለች ማለት ነው። ከደረጃ 4 በታች ውጤት የሚያመጡ ተማሪዎች አሁንም የክፍል ደረጃ ችሎታዎች እና ዕውቀት ሊያዳብሩ ይችሉ ይሆናል።

# የውጤት ሪፖርትን ማከፋፈል፡ ጀርባ

## 3) ልጅዎ ልዩ እውቀትን እና ችሎታዎችን ምን ያህል ተምሯል?

ተማሪዎች ስለ ጥንካሬያቸው እና ተጨማሪ ድጋፍ በየት ላይ ሊያስፈልጋቸው እንደሚችል በበርካታ ንኡስ ክፍሎች የበለጠ መረጃ ያገኛሉ። ለእያንዳንዱ ክፍሎች የቁጥር ውጤቶች የማይሰጥ ሲሆን፣ ሪፖርቱ ተማሪዎች የሚጠበቅባቸውን ወይም ከሚጠበቅባቸው በላይ ማሟላታቸውን፤ በመጠኑ ማሟላታቸውን፤ ወይም ከሚጠበቅባችው በታች ማሟላተቸውን ያሳያል።



3

## የ7ኛ ክፍል ሂሳብ ዝርዝሮች

የችሎታ ደረጃ
ደረጃ 4

### ስኮት ቁልፍ በሆኑ ፈተናዎች ችሎታው እንዴት ነበር?

በዚህ ፈተና በአጠቃላይ የደረጃ 4 ችሎታ ያሳዩ ተማሪዎች የሚጠበቅባቸውን የትምህርት ችሎታ አሳይቷል፣ ስለዚህ ለሚቀጥለው ክፍል ወይም ትምህርት ዝግጁ ነው። ይህ ክፍል በትምህርት ዓይነት ልጅዎ ደህና፣ በመጠኑ ደህና ወይም ደህና ያልሆነ መሥራቱን/ቷን ያሳያል።

| ዋናው ክፍል | ተጨማሪ እና አጋዥ ነገሮች | የሂሳብ መፍትሄ ፍለጋ አሰራርን መግለጽ | ሞዴል እና አፕሊኬሽን |
|---|---|---|---|
| የሚጠበቀው ወይም የበለጠ ✔ | ቤታች — | ለሚጠበቀው ምንም ያህል ያልቀረው ● | የሚጠበቀው ወይም የበለጠ ✔ |
| ራዲካልስ/ኤክስፖነንት፣ ፈንክሽንስ፣ ፔታጎራን ቲዮረም | የማይካፈሉ ቁጥሮች፣ ሾሊዩም የነጠብጣብ ዳያግራሞች | መፍትሄዎችን ማሳመንና መገምገም/የሌሎችን ምክንያቶች ማረም | ምልክቶችንና መሳሪያዎችን በመጠቀም ችግሮችን መፍትሄ መስጠት እና መወከል |

✔ የሚጠበቀውን ወይም ከሚጠበቀው የበለጠ ● የሚጠበቀውን መቅረብ — ከሚጠበቀው በታች

### የስኮት ችሎታ ከእኩዮቿ ጋር እንዴት ይወዳደራል?

4

የ7ኛ ክፍል ሂሳብ ፈተና ከወሰዱ የAnywhere MS ተማሪዎች ስኮት **60%** በላይ የተሻለ ውጤት አምጥቷል።

የ7ኛ ክፍል ሂሳብ ፈተና ከወሰዱ የDCPS ተማሪዎች ስኮት **50%** በላይ የተሻለ ውጤት አምጥቷል።

የ7ኛ ክፍል ሂሳብ ፈተና ከወሰዱ የDC ተማሪዎች ስኮት **70%** በላይ የተሻለ ውጤት አምጥቷል።

ካለፈው ዓመት የ6ኛ ክፍል ፈተና ጋር ሲነፃፀር፣ ስኮት ከDC ተማሪዎች **65%** በላይ የተሻለ ውጤት አምጥቷል።



### የሚቀጥለው ምንድነው?

ከልጅዎ አስተማሪ ጋር በሚነጋገሩበት የሚቀጥለው ስብሰባ፣ ይህንን ሪፖርት ያምጡ። የስኮትን አስተማሪ ሊጠይቁ የሚችሉት፡

- የዚህ ዓመት የስኮት ሂሳብ የመማር ሁኔታ እንዴት ነው?
- ስኮት እንዴት እየሰራ ነው?
- በዚህ ዓመት ከስኮት ጋር ለመስራት ይህንን መረጃ እንዴት መጠቀም እችላለሁ?
- ስኮትን ለማገዝ ምን መረጃ መጠቀም አለብኝ?

ተጨማሪ መረጃ የት አገኛለሁ?

- የስኮት ትምህርት ቤት እና ሌሎች ትምህርት ቤቶች ያገኙት ውጤት፡ OSSE.DC.gov ይጎብኙ ወይም DCPS በ(123) 456-7890 ይደውሉ።
- ፈተናው እንዴት እንደተቀረፀና እንዴት እንደሚለካ፡ PARCConline.orgን ይጎብኙ ወይም OSSE በ(202) 719-6500 ይደውሉ።
- እነዚህን ሪፖርቶች፤ ቤተሰቦች፣ አስተማሪዎች እና ትምህርት ቤቶች እንዴት እንደሚጠቀሙባቸው:

  OSSE.DC.gov/parcc ይጎብኙ ወይም በ(202) 719-6500 OSSE ይደውሉ።

5

## 4) ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ሲወዳደር እሱ/ሷ ውጤት እንዴት ነበር?

ይህ ሪፖርት የልጅዎ ውጤት በትምህርት ቤት ደረጃ፣ የሀገር ውስጥ የትምህርት ድርጅት ደረጃ፣ እና በዲስትሪክቱ ውስጥ ከእኩዮቹ ጋር ሲወዳደር ውጤቱ ምን ያህል እንደሰራ ያሳያል። በተጨማሪም፣ ያለፈው ዓመት የልጅዎ ውጤት በዲሲ አካባቢ ፈተናውን ከወሰዱ ተማሪዎች ጋር እንዴት እንደሚወዳደር ያሳያል።

## 5) የሚቀጥለው ምንድነው?

በውጤቱ ሪፖርት ላይ ያለው መረጃ የተማሪውን እድገት ለመለካት እና ችሎታን ለመገንባት መመምሪያ ለመስጠት የተዘጋጀ ነው። ይህ ክፍል የልጅዎን አስተማሪ ስለ አሰራሩ/ሯ ሊጠይቁ የሚችሉትን ጥቂት ጥያቄዎችን ያቀርባል። ተጨማሪ መረጃን የት እንደሚያገኙም ያካፍላል።

ግብዓቶች እና ድጋፍ

ልጅዎ ብቃቱን/ብቃቷን እንዲያሳድግ/እንድታሳድግ የሚያግዙ በርካታ ጠቃሚ ግብዓቶች እንዲሁም፣ የልጅዎትን የነጥብ ዘገባ በተመለከተ ከልጅዎት እና ከልጅዎት መምህር ጋር ለመወያየት ጠቃሚ የሆኑ ምክሮች ቀጥሎ ቀርበዋል፥

## ስለ ዲሲ የፒ.ኤ.አር.ሲ.ሲ ነጥቦች ወይም የፒ.ኤ.አር.ሲ.ሲ ምዘና የበለጠ ለማወቅ ይፈልጋሉ?

ስለ የፒ.ኤ.አር.ሲ.ሲ ምዘና እና የጋራ ዋና የእስቴት ደረጃዎች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የሚከተሉትን ድህረ ገጾች ይጎብኙ፥

- OSSE.dc.gov/parccበነጥብ ዘገባዎቹ፣ የፒ.ኤ.አር.ሲ.ሲ ምዘና እና በየጋራ ዋና የእስቴት ደረጃዎች ዙሪያ ስለዲሲ ውስን መረጃዎች ከፈለጉ።
- Results.OSSE.dc.gov የልጅዎት ትምህርት ቤት እና ሌሎች በዲሲ ውስጥ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች ያስገኙት ውጤት ምን እንደሚመስል መረጃ ለማግኘት።
- PARCConline.org ለወላጆች እና ለተማሪዎች ስለ ምዘናዎቹ እና ስለ ግብዓቶቹ መረጃ ለማግኘት።
- CoreStandards.org ስለ የጋራ ዋና የእስቴት ደረጃዎች የበለጠ ለማወቅ።

## አሁን የልጅዎትን የፈተና ውጤት አግኝተዋል፣ ቀጣዩ ነገር ምንድን ነው?

ልጅዎ በትምህርቱ/ቷ እንዲሻሻል/እንድትሻሻል ለማገዝ ይችሉ ዘንድ እነዚህን ግምገማዎች እንዲጠቀሙ የሚያግዙ በርካታ መርጃዎች አሉ፥

- GreatSchools.org የትምህርት ይዘት እና የክፍል ደረጃ ተኮር የሆኑ ቪዲዮዎችን የሚያቀርብ ሲሆን በቤት ውስጥ ከልጅዎት ጋር ትምህርት እና ልምምዶች ማካሄድ ይችላሉ።
- BeALearningHero.org በክፍል ደረጃ፣ በትምህርት ዓይነት እና በትምህርት ይዘት መሰረት ለዲሲ ግብዓቶችን የሚያበጁ ክህሎት ገንቢ ገጽን እና የትምህርት መሳሪያዎች ገጽን ጨምሮ ለወላጆች ብዙ ግብዓቶች አለው።
- PRC.PARCCOnline.org በተጨማሪም ከ 3ኛ እስከ 11ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች የመለማመጃ ፈተናዎች እና የናሙና ጥያቄዎች ያቀርባል።

## ከልጅዎ ጋር ስለ ውጤቱ/ቷ ለመነጋገር ይፈልጋሉ?

ወላጆች ከልጆቻቸው ጋር በመነጋገር ረገድ የተካኑ ናቸው። ቀጥሎ ስለ ልጅዎት የፈተና ውጤት በሚያወሩበት ጊዜ ማስታወስ ያለብዎት ጥቂት ጠቃሚ ነጥቦች ተዘርዝረዋል፥

- የፈተና ውጤቶች አንድ የአፈፃፀም ልኬት ብቻ ናቸው።
- በጠንካራ ጎኖቻቸው ላይ ትኩረት ያድርጉ።
- መሻሻል የሚሹ ዘርፎችን ተደራሽ ለማድረግ ስልቶችን ይወያዩ (ለምሳሌ፥ በቤት ውስጥ ሳይንሳዊ ሀሳቦችን መመርመር፣ ከአስተማሪ ጋር መስራት)።

## ከልጅዎ መምህር ጋር ስለ ልጅዎ ውጤት ለመነጋገር ይፈልጋሉ?

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ከልጅዎ መምህር ጋር የሚደረግ ውይይትን ለመምራት የሚረዱ ጥቂት ጥያቄዎች ናቸው፥

- በዚህ ዓመት በሂሳብ የልጄ የትምህርት ግቦች ምንድን ናቸው? በንባብስ?
- ልጄ በሂሳብ ትምህርት ክፍለ-ጊዜ እያሳየ/ች ያለው/ችው ብቃት ምን ይመስላል? በእንግሊዘኛ ቋንቋ ትምህርትስ?
- ልጄ እነዚህን ግቦች ለማሳካት በትምህርት ቤት እና በቤት ውስጥ ምን አይነት ተጨማሪ ድጋፍ ያስፈልገዋል/ጋታል?
- በእርሶ ምልከታዎች መሠረት፣ ልጄ በጥሩ ሁኔታ እየሰራ/ች ያለው ምንድን ነው? ለልጄ ማሻሻል የሚያስፈልጋቸው ዘርፎችስ የትኞቹ ናቸው?